“በአገር ጉዳይ ላይ ተሸናፊና አሸናፊ የለም!”

ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም

# የካቲት 12- እንጀራ ወይንስ ጊንጥ ?

ጥር 24 1999

የተወደዳቹሀ ውድ ኢትዮጵያውያን፡

በእነ ኢንጂነር ሃይሉ ሸዋል የወንጀል መዝገብ የተከሰሱ ኢትዮጵያዊያን የካቲት አሥራ ሁለት 1999 የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ይሰማሉ። ይህን ወሳኔ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የምንኖር በአሥር ሺህ ሚሊዮን የምንቀጠር ኢትዮጵያዊያን በአንክሮና በፀሎት እየተጠባበቅነው ያለ ውሳኔ ነው።

ኢሕአዴግ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲስፋፋ ትልቅ አስተዋጾ ማድረጉን ማንም የሚክደው ሐቅ አይደለም። የኢትዮጵያውያን ሁሉ አባት የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ከመውረዳቸው በፊት በመስከረም ወር 1999 ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በጻፉት ደብዳቤ ኢሕአዴግ የከፈተውን የዲሞክራሲ በር መልሶ መዝጋት እንደሌለበት ተማፅነዋል። [1] የእኚህ ሰላም ወዳድ ደብዳቤ ኢሕአዴግ ለመጀመሪያ ጊዜ ዲሞክራሲን እንዳስተዋወቀ በግልጽ ያስቀምጣል። ከግንቦት 7 1997 በፊት የነበሩት የፖለቲካ ክርክሮች፤ ይወጡ የነበሩት በርካታ ነጻ ጋዜጦች፤ በሚያዚያ 29 1997 ቅንጅትን በመደገፍ መንግስትን በመቃወም የተደረገው ታላቁና ታሪካዊው ሰልፍ ኢሕአዴግ ለወሰዳቸው መጠነኛ የዲሞክራሲ ሂደቶች እንደምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ኢሕአዴግ ለእነዚህ ዲሞክራሲያዊ አስተዋጾዎቹ ሊመሰገን ይገባዋል።

በአንጻሩም ኢሕአዴግ ስህተቶችን ሲሰራ፤ እራሱን ከሕግ በላይ ሲቆጥር ሊመከርና ሊገሰጽ አሊያም አልሰማም ሊወገዝ ይገባዋል። ያለፉትን ሁለት አመታት ብቻ ብንመለከት እንኳን ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ሃይሉን የሚሸረሽሩ ግዙፍ ስህተቶችን ፈጽሟል። የተፈጸሙት የሰብዓዊ መብት ረገጣዋዎችና ግድያዎች በአበይትነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

በሰኔ ወር 1997 የምርጫ ቀጠራውን ሂደት በመቃወም በተነሳው አለመረጋጋት በኮተቤ አካባቢ ከደህንነት ሃይሎች በተተኮሰ ጥይት የተገደለችዋን የወጣት ሽብሬ ደሳለኝን ፎቶ በጋዜጦች ላይ ስመለከት ውስጤን ታላቅ ሐዘን ነበር የሞላው። በዚያኑ ቀን የተግባረ እድ ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊሶች በሰደፍ ሲደበደቡም ተመልክቻለሁ።

## “በአገር ጉዳይ ላይ ተሸናፊና አሸናፊ የለም!”

*ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም*

ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በአሥመራ ለኤርትራ ነጻ መንግስት እዉቅና በመስጠቱ “የኢትዮጵያ አንድነት አይደፈርም“ በሚል መፈክር ስር ባደረግነዉ ሰላማዊ ሰልፍ “ኢሰፓዎች ፤ ደህንነቶች” እየተባልን የተርከፈከፈብን የተኩስ እሩምታ፤ በዚያም የተገደሉት ሃያ ዘጠኝ ወጣት ኢትዮጵያዊያን ትዝ ብለዉኝ ነበር። “ያኔስ ኢሕአዴግ ገና ሕዝብ የማስተዳደር ልምድ አልነበረዉም” ብለዉ አንዳንዶች ሰበብ ሊሰጡ ይችሉ ይሆናል። አሁን ግን ለአሥራ አራት አመት አገር ያስተዳደረ የፖለቲካ ድርጅት እንዲህ አይነት የጭካኔ ሥራ በዜጎቹ ላይ ሲፈጽም ማየት ብዙዎቻችንን አስቆጥቷል።

ኢትዮጵያ ዉስጥ የታዩት አንጻራዊ የኢኮኖሚ መሻሻሎች፤ የተገነቡት አዳዲስ ትምህርት ቤቶችና መንገዶች፤ በኢሕአዴግ የተሾሙት የቀድሞ የመዲናችን ከንቲባ ክቡር አቶ አርከበ እቁባይ በአዲስ አበባ ከተማ ያሳዩት ተጨባጭና የሚታዩ ለዉጦች ... በአንዳንዶቻችን ዘንድ ለኢሕአዴግ መጠነኛ ከበሬታ እንዲኖረን አድርጎን ነበር።

ያለፈዉ አመት ያየነዉ አሳዛኝ የአገራችን ሞዕራፍ ግን በኢሕአዴግ ላይ በቀይ ቀለም የተቀባ ትልቅ የጥያቄ ምልክት እንድናደርግ አስገድዶናል። በሚሊዮን የምንቆጠር ኢትዮጵያዉያንም ከዝምታዉ አለም ወጥተን የዜጎችን ደም በከንቱ ያፈሰሱት ለሕግ እንዲቀርቡ፤ የተቋረጠዉ የዲሞክራሲ ሂደት እንዲቀጥልና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ደም ማፍሰስ በኢትዮጵያ እንዲያበቃ ለመታገል ቆርጠን ተነስተናል። ሰላማዊ ዜጎች ሲገደሉ ትግል አይሞትም። የእነ ሽብሬ ደሳለኝ ደም በከንቱ አልፈሰሰም። እኛን ካንቀላፋንበት ቀስቅሶናል። በኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማሪያም ይመራ የነበረዉ ጦር በሃዉዜን ትግራይ ሕዝብ ላይ ያደረገዉ ጭፍጨፋ የሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይን ተዋጊ አባላት በበርካታ እጥፍ አሳድጎት እንደነበረ የማይዘነጋ ነዉ። የሃይል እርምጃ በቀልንና ጥላቻን በመፍጠር ችግሮችን ያባብሳል እንጂ አንዳች መፍትሄ አያመጣም።

በስህተት ላይ ስህተት በጥፍት ላይ ጥፋት እንዳይደራረብ፤ አገራችንን መዉጣት ወደ ማትችልበት ወደባሰ ከፍተኛ አዘቅት ዉስጥ እንዳትገባ ብስለትና ማስተዋል ያለበትና ሕዝቡን ለእርቅና ለሰላም የሚጋብዝ እርምጃዎች በኢሕአዴግ በአስቸኳይ መወሰድ እንዳለበት እሳስባለሁኝ። ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም በቅርቡ ከቃሊቲ እሥር ቤት ለኢትይጵያ ሕዝብ በጻፉት ግልጽና ታሪካዊ ደብዳቤ ለአገራችን መፍትሄዉ ዉይይት ብቻ እንደሆነ አስምረዉበታል። “በአገር ጉዳይ ላይ አሸናፊና ተሸናፊ የለም” ይሉናል እኝሁ የተከበሩ ኢትዮጵያዊ የሕግ መምህር። [2] ለዉይይት ለሰላም ለእርቅ መቼም ቢሆን በሩ ሊዘጋ አይገባም። ተስፋ በመቁረጥ የእልህ እርማጃዎችን መዉሰደ ለአገራችን ስር የሰደደ ትልቅ ጉዳትን የሚያመጣ ነዉ። <u>በፍጥነት ወደ ገደል</u>

**<u>እየገሰገሰ ያለዉን ባቡር ለማስቆም፤ አቅጣጫዉንም ወደ ቀናዉ መንገድ ለማስቀየር የሚደረገዉ ጥረት መጧጧፍ ይኖርበታል። አለበለዚያ ከባቡሩ ጋር ገደል ዉስጥ ተወርወረን አንዳችም ሳንተርፍ እናልቃለን። ታዋቂዉ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዳሉት “በወንድማማችነት ተከባብረን ካልኖርን ሁላችንም እንደ እብዶች እንጠፋለን።”</u>**

“ጠጅ በብርሌ፤ ነገር በምሳሌ” ተብሎ እንደተተረተዉ ሐሳቤን በግልጽ እንዲያብራራልኝ የአንድ የእሥራዔል ንጉስን ታሪክ በአጭሩ ለመግለጽ እሞክራለሁ። [3]

ሰባት መቶ ምዕተ አለም አካባቢ የቀዳማዊ ሚኒሊክ አባት ንጉስ ሰለሞን ሲሞት ልጁ ሮብዓም በምትኩ በእሥራኤል ላይ ነገሰ። ሕዝቡም የተጫነባቸዉ ቀንበር እንዲቀነስላቸዉ ጥያቄ አቀረቡ። ንጉሱም የሶስት ቀን ቀጠሮ ሰጥቷቸዉ አሰናበታችው። አማካሪዎችን ሰብስቦ ምን መደረግ እንዳለበትም መከረ። በእድሜ ባለጠጋ የሆኑት አረጋዉያን ሕዝቡን እንዲሰማ፤ ቀንበራቸዉን እንዲቀንስና በትህትና ራሱን እንዲያቀርብ አሳሰቡት። “ሕዝብ ከወደደህ በሰላም ይገዛልሃል፤ በአገሪቷም ብልጽግና ይበዛል” አሉት። በአንጻሩም ወጣት አማካሪዎቹ በፍጹም ሕዝቡን መስማት እንደሌለበት፤ ይህን ካደረገ እንደ ደካም እንደሚቆጠር አልፎም እንደሚናቅ ተናገሩ። “እንደዉም ቀንበራቸዉን ብታበዛ ከአሁን በኋላ አርፈዉ እንዲቀመጡ ጥሩ መቀጣጫ ይሆናቸዋል” አሉ።

ለንጉሱ ሁለት አማራጮች በግልጽ እንደተቀመጡለት እናያለን። ሕዝቡን ከጎኑ ማሰለፍ ወይንም ሕዝቡን ማስቆጣት? የአስተዋይ ሽማግሌዎችን ምክር መስማት ወይንም የወጣቶችን የስንፍና ምክር መቀበል? በአገሪቷ ሰላምን ማሰፈን ወይንም ጦርነትና ሁከትን መቀስቀስ?

ንጉሱ ሮብዓም ለሕዝቡ “ታናሺቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች። አባቴ በአለንጋ ገርፏችኋል፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋቹሃለሁ” በማለት የንቀት መልስ ለሕዝቡ መለሰ። “ሕዝቡ የት ይደርሳል?” ብሎ በማሰብ ልቡን በትዕቢት ሞላ። ለሰላምና ለእርቅ፤ ለፍትህና ለመልካም አስተዳደር በሩን ሙሉ ለሙሉ ዘጋ። በወሰደዉም ማስተዋለ ቢስ እርምጃ የሕዝቡን አመጽ ቀሰቀሰ። ያስተዳድራቸዉ ከነበሩት አሥራ ሁለት ክፍለ አገራት አሥሩ ለእርሱ አንገዛም ብለዉ ሸፈቱ። አገሪቷ ለሁለት ተከፈለች። ንጉሱ በነገሰ በአምስተኛዉም አመት በግብጽ ፈርኦን ሺሻቅ በቀላሉ ተወሮ የዘመኑ መሳለቂያና የታሪክ ማፈሪያ ሆነ። በነገሰባቸዉ አመታት ሁሉ የሰላምን አየር ሳይተነፍስ ከዚህ አለም በሞት ተቀጠፈ።

## "በአገር ጉዳይ ላይ ተሸናፊና አሸናፊ የለም!"

*ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም*

የእስራዔል ሕዝብ ለርዕሰ ብሄራቸዉ ብሶታቸዉን እንዳቀረቡ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብም ለኢሕአዴግ መንግስት ጥያቄዎቹን ያቀርባል። "በፍርሃት መኖር አንፈልግም። የመረጥናቸዉ የቅንጅት ተመራጭቻችን፤ የነጻዉ ፕሬስ አባላትና የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ያለ አንዳች ቅድመ ሆኔታ ይፈቱልን። ለዲሞክራሲ ሱሰኞች ለአምባገነንነት አለርጂክ ሆነናል" እያለ ድምጹን ያስተጋባል።

የኢሕአዴግ የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም አንዳንድ የኢሕአዴግ ደጋፊዎች በውጭ ያለዉ አክራሪዉ ዳያስፖራው ነዉ እንጂ ሕዝቡ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሰላምና በመረጋጋት ነዉ የሚኖረዉ ይሉናል። የእሥራዔል ሕዝብ የግፍ አስተዳደርን :" እምቢ አሻፈረኝ" እንዳለም ኢትዮጵያዉያን መብታቸዉ ተገፎ ቁጭ እንደሚገዙ ማሰብ ሞኝነት ነዉ።

እርግጥ አንዳንድ በዉጭ አገር የሚኖሩ ቅንጅትን የማይወክሉ ቅንጅት ነን ባዮች የሚናገሩት ንግግርና የሚጽፉት ጽሁፍ ገንቢ እንዳልሆነ የታወቀ ነዉ። የኢሕአዴግ አባላትን አራዊቶች ብሎ መሳደብ የመንግስት ባለሥልጣናትን ለይቶ በጨዋነት ከመዉቀስ ይልቅ በጅምላ አጠቃሎ መፍረጅ ከቅንጀት መርሀና መንፈስ ዉጭ የሆነ የኋላቀርነት ፖለቲካ ነዉ። እነዚህ ግለሰቦች በምንም አይነት መመዘኛና መስፈርት ቅንጅትን አይወክሉም። **ቅንጅት የዲሞክራሲ ዋና መርህዎች እስከተጠበቁ ደረስ ከኢሕአዴግ ጋር አብሮ መሥራት የሚፈልግ ፤ የኢሕአዴግ አባላትን የሚያከብርና በፍቅር በወንደማማችነት በአንድነትና በጨዋነት ላይ የተመሰረተን ፖለቲካ የሚያራምድ ነዉ።**

የዳያስፖራዉ ሕብረተሰብ እንቅስቃሴ እንዳለ ሆኖ (ወደፊት የምንነጋገርበት ጉዳይ ሊሆን ይችላል) በአገር ቤት ያለዉ ወገናችን የመሰብሰብና የተቃዉሞ ሰልፍ የማድረግ ሕገ መንግስታዊ መብቱን ቢነፈግም ባገኛቸዉ አጋጣሚዎች ሁሉ የመብት ጥያቄዎችን ከማቅረብ ታክቶ አያዉቅም። በ1998 እና 1999 የጥምቀት በዓል ሲከበር ፤ በመስከረም 1999 ደመራ በመስቀል አደባባይ ሲበራና በቅርቡ ተደረጎ በነበረዉ ታላቁ ሩጫ በከፈተዉ አጋጣሚ ሕዝቡ ጥያቄዎቹን በግልጽ አስቀምጧል። "መሪዎቻችን ይፈቱ " የሚለዉ መፈክሩ ተስተጋብቷል። በተለያዩ ጊዚያትም በአዲስ አበበ፤ በጂማ፤ በናዝሬት በድሬደዋ፤ በደሴ፤ በአምቦና በሌሎች በርካታ ከተሞች ለረጅም ጊዜ የተደረጉት የተማሪ ተቃዉሞዎች ሕዝቡ እንዳልተመቸዉ አሁን በሥልጣን ላይ ካለዉ መንግስት ጋር የተራራቀ መሆኑን ያሳያል።

ታዲያ የሕዝቡን ድጋፍ ለማግኘት ኢሕአዴግ ምን ማድረግ አለበት? የሕዝቡን እምነትና ፍቅር ለማግኘት በርካት መልካም አጋጣሚዎችን ኢሕአዴግ ከዚህ በፊት ቢያበላሽም በየካቲት 12 1999 ከገባበት ቀዉስ ማምለጥ የሚችልበትና እንደገና

## “በአገር ጉዳይ ላይ ተሸናፊና አሸናፊ የለም!”

*ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም*

ከሕዝቡ ጋር የሚታረቅበት ትልቅ አጋጣሚ ተከፍቶለታል። ይህ አጋጣሚ ኢሕአዴግ ካልተጠቀመበት የመጨረሻው አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ብዬ በጽኑ አምናለሁ። ቀን ሳለ መሰራት ያለበት ነገር ካልተሰራ ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ በጨለማ እየተሯሯጡ ገደል መግባት ብቻ ነው ትርፉ።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም፣ ዶ/ር ሰለሞን ተርፋና ዶ/ር ሰብሃት እንዲሁም ሌሎች ስምንት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን “ይቅር ለእግዚአብሄር” በሚል መርህ ብሄራዊ እርቅ የሚመጣበትን ኢትዮጵያዊ አማራጭ በ1991 ማቅረባቸው የሚታወስ ነው። [4] ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማሪያም ከአራት ሰዓት በላይ በፈጀው ንግግራቸው ፡ “የአገር ጉዳይ የባለና የሚስት ጉዳይ አይደለም” በማለት በአሥራ አንዱ ምሁራን የቀረበውን የዕርቅ ሐሳብ አጣጣሉት። ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መንግስታቸው ተሸርሽሮ ወደቀ። እግዚአብሄር ትዕቢታቸውን አይቶ አዋረዳቸው።

አሁንም ኢሕአዴግ ከደርግ እንዲማርና የተከፈተለትን መልካም አጋጣሚ እንዲጠቀምበት አጥብቄ እማጸናለሁ። <u>በጉጉት በሚጠበቀው በዚያን እለት በቃሊቲ የታሰሩ የሕሊና እሥረኞች ላይ “ወንጀለኛ” የሚል ብይን ፍርድ ቤቱ ቢሰጥ ኢሕአዴግ ሕዝቡን በጊንጥ ለመግረፍ መወሰኑን በገሃድ ያመለክታል።</u>

የካቲት 12 ኢሕአዴግ ከስህተቱ ተምሮ ወደ እርቅ ይመጣል ወይንስ በጭፍን የሕዝብ ሰቆቃ እንዲቀጥል ይፈቅዳል? እራሱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያመጣውን ዲሞክራሲ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይቀብረዋል ወይንስ ለዲሞክራሲ መስፋፋት ያለውን ታማኝነት ያረጋግጣል? “መሳሪያ እስካለኝና አሜሪካኖችን በፀረ ሽብርተኝነት ሽፋን ከጎኔ እስካሰለፍኩኝ ድረስ ይህንን ህዝብ ረግጬ ብገዛው ምንም አልሆንም” ብሎ ኋላቀረነትን ይመርጣል ወይንስ በጠመንጃ መፍትሄ እንደሌለ ተረድቶ በአገራችን ችግሮችን በሃይል የመፍታት ባህል እንዳበቃ ያውጃል? ምርጫውን ለኢሕአዴግ ባለ ሥልጣናት እተዋለሁ።

ከአንዳንድ ማዕዘኖች “በቃሊቲ ያሉ እሥረኞች ጉዳይ በፍርድ ቤት የተያዘ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሕግ አለ።” ሲባል እሰማለሁ። ኢሕአዴግ የቃሊቲ እሥረኞችን እንዲፈታ ስጠይቅ በኢትዮጵያ ያለውን ሕግ በመናቅ ወይንም ወደ ጎን በማድረግ አይደለም። ነገር ግን ሕጋዊ የመፍትሄ አማራጮች አሉ ብዬ ስለማምን ነው።

አንዱ አማራጭ አሁኑኑ ተግባራዊ መሆን የሚችል አማራጭ ነው። ከአሁን እስከ የካቲት አሥራ ሁለት ባሉት ጊዜያት አቃቤ ሕጉ ከፈለጉ ክሱን ሊያነሱት ይችላሉ። አቃቤ ሕጉ በፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥሉ የሚያስገድዳቸው አንድም የሕግ አንቀጽ

# “በአገር ጉዳይ ላይ ተሸናፊና አሸናፊ የለም!”

*ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም*

የለም። በብዙ ቦታ አቃቢ ሕጎች  አዲስ መረጃ ካገኙ ወይንም ከተከሳሽ ጠበቆች ጋር ውል (plea bargain) ካደረጉ የክሳቸውን ፋይል ማዘጋት የተለመደ የሕግ አሰራር ነው።

አቃቢ ሕጉ በፍትሕ ሚኒስትሩ ይታዘዛሉ። ፍትሕ ሚኒስትሩ ደግም የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የካቢነ አባል ናቸው። ሥለሆነም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ፍቃዳቸው ከሆነ ነገ በቃሊቲ ያሉ እሥረኞች እንዲፈቱ ማድረግ ይችላሉ። ሕጉ በጭራሽ አይከለክላቸውም።

ሁለተኛው አማራጭ በየካቲት 12 የዕለቱ ቀን ሊደረግ የሚችል ነው። ፍርድ ቤቱ ቃሊቲ ባሉ እሥረኞች ላይ የፍርድ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያኔውና ምህረት (amnesty) በመስጠት በሕጋዊ መንገድ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ መቀልበስ አያቅታቸውም።(አሁንም ፍላጎቱ ካለ)

ከሕግ ጋር ምንም ባልተገናኘ መልኩ ኢሕአዴግ ውስጥ ካለው ፖለቲካ አኳያ ድንገት ጠቅላይ ሚኒስትር መልስ ዜናዊ እሥረኞችን መፍታት አይችሉ ይሆናል የሚል ግምትም አንዳንዶች ሊኖራቸው ይችላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብዙዎቻችን እንደምናስበው ለብቻቸው የሚወስኑ አምባገነን ላይሆኑም ይችላሉ።

ታዲይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰላምን እየፈለጉ ፓርቲያቸው አግዷቸው ከሆነስ? አሁንም ኳሱን ከእርሳቸው ሜዳ አላርቀውም። ከፓርቲ ይልቅ አገርን እንዲያስቀድሙ አሳስባቸዋለሁ። ድርጅታቸው የእርሳቸውን መሪነት የማይቀበል ከሆነ ወደፊት ለሚፈጠረው ችግር ተጠያቂ እንዳይሆኑ ለሕዝብ አሳውቀው ከሃላፊነታቸው በፈቃዳቸው (resignation) መነሳታቸው ብቸኛ አማራጫቸው ይሆናል። ይህንንም ካደረጉ ለጊዜው ሊዋረዱ ይችላሉ። የማታ የማታ ግን የሚያስከብራቸው ድርጊት እንደሚሆን ጥርጣሬ የለኝም።

ደግሞም ለመጀመሪያ ጊዜ በሰላም ስልጣናቸውን በመልቀቃቸው በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ሰው በመሆን ታሪክን የመሥራት እድልም ያገኛሉ።

ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም እንደጻፉት “አገራችን በብዙ ፖለቲካዊ ኦኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተተብትባለች። በአንገታችን ዙሪያ የተጠመጠሙ ማነቆዎች እየጠበቁ እየሄዱ ነው። ድንገትም ሳናውቀው ጉሮሮአችንን አንቀው እስትንፋሳችንን ሊቆርጡት ይችላሉ”. [2] በመቶ የሚቆጠሩ ተገድለዋል። በአሥር ሺህ የሚቀጠሩ ታስረዋል። በሚሊዮን የሚቆጠረው ሕዝባችን በፍርሃት አቀርቀሮ በመኖር ላይ ይገኛል። እንኳን የሰለጠኑት የምዕራባውያን አገሮች ትናንትና ነጻ የወጡት እነ ጋና

ሴኔጋል የመሳሰሉት የአፍሪካ አገሮች እንኳን የትናየት ጥለዉን ሄደዋል። አገር እያለን ተሰደናል። ምግብ እያለን ተርበናል። ክብር እያለን ተዋርደናል።

ሁላችንም በቅንነት አገራችንን ለመርዳትና ከውርደቷ ለማንሳት እንነሳ። አሁንም ዶ/ር ያዕቆብ እንደጻፉት "ለአገራችን ጥቅም መቆም ብቻ ከሆነ በእኛና በኢሕአዴግ መካከል ያለው ልዩነት ትንሽና በቀላሉ ሊፈታ የሚችል ነው።" [2]

**እንግዲህ በፊታችን እንጀራና ጊንጥ ተቀምጧል። ዛሬ የምንወስነው ውሳኔ የነገውን ህልውናችንን ይወስናል። እንጀራውን መርጠን ከርሱም ተመግበን በሕይወት መኖርን እንመርጣለን ወይስ ጊንጡን መርጠን እራሳችንን እናጠፋለን?**

"እሺ" ለእንጀራ "እምቢ" ለጊንጥ የምንል ሕዝቦች ያድርገን !
እግዚአብሄር አገራችንን ይፈውሳት !

ግርማ ካሳ
ቺካጎ
(muziky68@yahoo.com)

[1] – http://www.mesfinwoldemariam.com/docs/MWM_OpenLetter_PM_2005.pdf
[2] – http://www.aigaforum.com/yacob.pdf
[3] – The First Book of Kings, Chapter 12
[4] – http://www.mesfinwoldemariam.com/docs/MWM_EthiopianStudies_1991.pdf